# ዐማራና ዐማርኛ

ታሪክ የሰውን ልጅ ማኅበራዊ ኑሮ፣ ድርጅቶቹን፣ ባሕሉን፣ ሃይማኖቱን ወዘተረፈ በተጨባጭ ማስረጃዎች ማለትም በጽሑፍ፣ ሰነድ፣ በጥንት ቅርስ ፍራሽና ቅሬት፣ በተውፊት (አፈታሪክ) ያለፈውን ክንውን ከጊዜና ስፍራ አንጻር አገናዝቦ የሚያሳይ የዕውቀት ዘርፍ ነው።

በመሆኑም የታሪክ ጥናት ሁለት ዓቢይ ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው ቅድመ ታሪክ ሲባል ሁለተኛው ዘመነ ታሪክ ይባላል። የሥነ ጥንት ቅርስ ጥናት በምድር ውስጥ የተቀበሩ ፍርስራሽ ቅርሶችን፣ ቅሪቶችን የሚመረምር በአብዛኛው በቀደመ ታሪክ ክፍል ዘርፍ ላይ ያተኩራል። ታሪካዊ ማስረጃዎችን የጽሑፍ ሰነዶች፣ የሕንፃ፣ የእርሻ፣ የንግድ፣ የእደ ጥበባት ክንዋኔዎች፣ የሃይማኖት፣ የማኅበረሰብ መስተጋብራትን በጊዜና ስፍራ ተለይተው የሚታወቁበት ዘመነ ታሪክ ነው። ስለ ኢትዮጵያዊ ዐማራ ሕዝብ ታሪክ በተጠቀሰው የአጠናን ስልት መሠረት መረጃዎችን በመገናዘብ ይቀርባል። በሃይማኖት ሳቢያ፣ በይሆናል ግምትና መላ ምት የተጠናቀሩት አመለካከቶች ይቃኛሉ። ያማራው ሕዝብ ታሪክና ሥልጣኔ የአፍሪቃ አባይ ሸለቆ ሕዝቦች አካልና መሠረት ለመሆኑ በሰፊው ይገለጻል።

የኢትዮጵያን ሕዝብና መንግሥት ረጅም ታሪክ በሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ በተመለከተ በዘመን ኢምፔሪያልዝም የምዕራብ አውሮፓ ቅኝ ገዥዎችና ተስፋፊዎች በተለይም የጀርመን፣ የጣሊያን፣ የፈረንሳይና እንግሊዝ ምሁር ተብዬዎችና አገር ሰላይ ሚሲዮናቶቻቸው ሁሉ በነጭ ዘር የበላይነትና የአሰልጣኝነት ተልዕኮ በፍጹም የዘረኝነት አስተሳሰብ እየተመሩ እጅግ ብዙ ትርኪ ምርኪ አጠናቅረዋል። የጥቁር ሕዝብ ዘርያዎችን በዝቅተኛነት ደረጃ መድበው በያለበት በአረመኔ ጭፍጨፋ፤ ወረራና ዝርፊያ ከምድረ ገጽ ላይ ለመጥፋት ሞክረዋል።
ለምሳሌ በአውስትራሊያ የታስማኒያ ጥቁር ዘርያዎች በጭራሽ ከወደሙት ሕዝቦች ወገን እንደሆኑ መጥቀስ ይቻላል። (Patric Brantlinger: Dying races: rationalizing genocide in the ninteenth centrury (1995) ,PP.43-56)

በኢትዮጵያ ምድር የሚገኘውን ጥንታዊ የጥቁር ሕዝብ ሥልጣኔ ከእሲያ የአረብ ሠርፀ ምድር የፈለሱ አበሻና እግአዚያን የተባሉ "ሴማውያን ነገዶች" ፈጠራ ነው እየተባለ ተስፍፏል፣ ዛሬም እንኳ እንበለ እፍረት ያናፍሳሉ፡ የኢትዮጵያን ጥቁር ሕዝብ ሥልጣኔ አፍሪቃዊ ምንጭና መሠረት ዓይናቸውን በጨው አጥበው ሸፍጠዋል፡ ተመሳሳይ ጽሑፍና ሕንፃ በየመንና በአክሱም ግዛት ውስጥ ስለተገኙ ብቻ የሳባውያን ቅኝገዥዎች የአክሱምን ሥልጣኔ ፈጠሩ የሚባል ከሆነ ስለምን የጥንት ግሪካውያን በጠቅላላው ከምደረ ግብፅ የአፍሪቃ ኩሻውያን ጥቁር ሕዝብ ሥልጣኔ መቅዳታቸው ወይም ቅኝ ግዛት መሆናቸው በሰፊው መነገርና መታወቅ ይኖርበታል። ነገር ግን ከሁሉም በተቀዳሚ መታወቅ ያለበት ሐቅ በጥንት የመን ሳባውያን ሴማዊ ሳይሆኑ እንዲሆኑ ተድርጎ ውሸት መነዛቱን ነው። የሳባ፣ የሕማርያ፣ የቀጠባን፣ የሚናን ቋንቋዎች ከአረብኛ ይሁን ከዕብራይስጥ ጋራ በጭራሽ አይዛመዱም። በየመን የተገኙት አጭር የጽሐፍ ሰሌዳዎች እንጂ ረጃጅም የታሪክ ዘገባ ለምሳሌ እንደ የግብፅ ሂሮግሊፊስና እንደ አጤ ኢዛና ዓይነት ሰሌዳ አልተገኘም።

የአረብኛ ቋንቋ በየመን የተስፋፋው ከእስልምና ሃይማኖት ጋራ በሰባተኛው ክፍለ ዘመን ነው። ሁሉም የጥንት የመን ቋንቋዎች ከኩሻዊ ቋንቋ ቤተሰብ ሲሆኑ መነሻቸውም ከሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ ነው። በደቡብና ደቡብ ምዕራብ የሚኖሩት ሳባውያንና ሌሎቹ የየመን ጎሳዎች ሁሉም የጥቁር ዘርያ ኩሻዊ ነገዶች በቋሚ ሰፋሪነት መንደርና ከተማ ግንብተው ገበሬዎችና ነጋዴዎች ሆነው ሲኖሩ በአረቢያ በርሃማው ሰሜናዊ ምሥራቅ ክፍል እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ የሚኖሩት ሴማዊ ዘላኖች የአረብና እብራዊ ጎሳዎች ነበሩ። እንኳን ደቡብ አረቢያ ሠርፀ ምድር ይቅርና የባቢሎን፣ የከለዳውያን፣ የሱመሪያውን፣ የኢላምና የጥንት ሕንድ ሁሉ የጥቁር ሕዝብ ዘርያ የኩሻውያን ሥልጣኔ መሆኑ የታወቀ ነው። (http:www.sacred-texts.com/ afr)

የ18ኛው-ና የ19ኛው ክፍለ ዘመን የምዕራብ አውሮፓ ልሂቃን ለቅኝ ገዥነትና ተስፋፊነት፤ ለነጭ ዘር ያሠልጣኝነት ተልእኮ ምኞትና ቅዠት ተሰማሚ ትርጉምና ግኝት አቀናብረዋል። ታሪክን አፋልሰው ቅራቅንቦ ተረት ፈጥረዋል፡ ኢትዮጵያ በአፍሪቃ አህጉር ያውሮፓ ኢምፔሪያሊስቶችን ወረራና ከበበባ ተከላክላ፤ ነፃነቷን በልጆቿ የጋራ መሰዋትነት ጠብቃ የቆየች፣ በዓለም ላይ ብቸኛ የጥቁር ሕዝብ አገር በመሆኗ ምክንያት የምዕራብ አውሮፓ ዘረኞች የጥንት ግብፅን ሥልጣኔ፣ ቋንቋና ባሕል ከአውሮፓ ነጭ ዘር ተብዬው ክልስልስ ወገን ለማዛመድ እንደጣሩት ሁሉ በኢትዮጵያ ምድር የሚገኘውን ጥንታዊ ሥልጣኔ መካድ ሰለማይቻላቸው ሌላው አማራጭ የአረቢያ ሴማውያን ሠፋሪዎች የአክሱምን መንግሥትና ሥልጣኔ ፈጠሩ ብሎ በታሪክ ስም መዋሸትን መርጠዋል። የኢትዮጵያ ምድርና ሕዝቡም ከጥንት ግብፅ፡ ከኑቢያና ሌሎች አጎራብች ሕዝቦች ጋራ የነበረውን ቀጥተኛ መልክዐ ምድራዊ ዝምድናና የረጅም ዘመናት የጠበቀ ግንኙነት ሸፍጠው ከአረብያ ብቻ ፈለሱ ሰለተባሉት አሠልጣኞች የውሸት ሰንክሳር ደጉሰዋል። ዘረኞች ዓይናቸውን በጨው አጥበው ስለ ስለኢትዮጵያ "ታሪክ" ሲጽፉ የጥንት ኢትዮጵያ በአፍሪቃ ከፈርኦን ግብፅ ጋራ ምንም ዓይነት ግንኙነት እንዳልነበራትና በዢግሮሊፐስ ጽሑፍ ሰለ ፑንትና የቅመማቅመምና አማልክት የአበሻ አገር ከ2500 - 600 ዓ.ዓ የተመዘገበውን እጅግ ብዙ ሰነድ ዋጋ እንደሌላቸው ጀርመናዊ አኖ ዲልማን ስለ አክሱም ግዛት አጀማመር / A. Dilmann: Ueber die Anfaenge dei Axumitischen Reichs ,Berlin 1879, P.182)፤ የእንግሊዙ ዋሊስ ቡጁ ( E.A.W Budge: Ethiopia and the Ethiopians, (Londor 1928),P.130; የጣሊያኑ ኮንቲ ሮዘነ (Conti Rossini: Sugli Habashat, (Rome: 1906), PP.39-59) etc. የውሸት ዝባዝንኪ አጠናቅረዋል። በተለይ እንግሊዛዊው ዋሊስ ቡጂ በደቡብ ሸዋ በምደረ ጉራጌ ጥያ ከሰዶ እስከ ሲዳሞ ቱርካና ሐይቅ ድረስ ቆመውና ወድቀው የሚገኙትን የቁም ድንጋይ ሐውልቶችን በፈረንሳዩ ቄስ አዚያስ ተጎብኝተው የተመዘገቡትን፤

<< የታሪክ ሰንድ አይሆኑም፣ የተሠሩትም በአረቦች ነው፣ ኢትዮጵያውያን ምንም ነገር አልፈጠሩም። ላሊብላና አክሱምንም ወዘተ ሁሉ የሠሩት ከግብፅና ግሪክ የመጡ ሥልጡኖች ናቸው። ኢትዮጵያውያን ከወታደርነት ሥራ በስተቀር ለምንም ነገር ችሎታ የለቸውም>> እያለ ጽፏል።

ሌላው ወሻካች ስፔንሰር ትሪሚንግሃም (1952) የተባለውም እንግሊዛዊ የአረብ ታሪክ ሊቅ ተብዬ ትርክምርኪውን ሲያራግብ አኖ ሊትማንም (1875-1958) የተባለውን የዘረኛነት አመለካከት ዋና አቀንቃኙን በመጥቀስ አናፍሷል። የሴማውያን አበሻና አጋአዚያን ተብዬ ነገዶች ከአረቢያ ሠርፀ ምድር ፍልሰው በኢትዮጵያ አምባ ምድር የመስፈር የፈጠራ ተረት ተረት በዘመናዊው የሥነ ቋንቋና በጥንት ቅርሳቅርስ ፍርስራሽ ጥናት ውድቅ ተደርጓል። በዚህም መሠረት አሜሪካዊው ዩሴፍ ግሪንበርግ የቋንቋ ምሁር የአፍሪቃን ቋንቋዎች እአአ 1955 ዓም በአደረገው ምደባ የአንዱ ዘርፍ አፍሮ-እሲያ የሚገኘውና ምንጩ ኢትዮጵያ መሆኑን እንዲሁም ሌሎች የአፍሪሲያ ቋንቋ ቤተሰብ ተመራማሪዎች እነ ጀ ሁስዶን (Geolingustic evidence for Ethiopian Semitik Prehistory, Abbay No 9 (1978), PP. 71-72 ወዘተረፈ እንዳረጋገጡት በኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ከቅደም ታሪክ በፊት ቢያንስ 2ሺህ ዓመታት በላይ ሴማዊ ቋንቋ መነገሩ ተረጋግጧል። በመሆኑም አገውኛ፣ ግእዝ፣ ዐማርኛ፣ ጉራግኛ፣ ጋፋትኛ በዚሁ ስፍራ በአፍሪቃ የስምጥ ሸለቆና የኢትዮጵያ አምባዎች የተፈጠሩ ናቸው። እንዲያውም የጉራጌኛ ቋንቋዎች የቅድመ ሴማዊ መነሻ (Proto Semitic) ምንጮች እንደሆኑ ተገምቷል። (Appleyard, 2003)

ዘረኞች የአክሱምን ጥንታዊ ሥልጣኔ ዘመናት እጅግ በጣም ቀናንሰው በአራተኛው ክፍለ ዘመን ተጀመረ እያሉ ለፈጠራ ውሸታቸው እንዲስማማ አድርገው ቀምረውታል። ነገር ግን የአረብ ሠርፀ ምድር ጥናት ሊቂ የሆኑት ወይዘሮ ጃክሊን ፒረነ (1956) በትክክል እንዳስቀመጡት በተቃራኒው የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ወደ አረብ የመን እንደተሻገረ፣ የሳባ አሰልጣኞችን ቀይ ባሕርን ተሻግሮ በሰሜን ኢትይጵያ የመስፈር ተውኔት የነ ኮንቲ ሮዘነና ብጤዎቹን ተረት ተረት በተጨባጭ ሰንድ ጠጊዜና በስፍራ ለይተው ዘቅዝቀውታል።

ያውሮፓ ዘረኞች ተረት ባፍጢሙ ተደፍቷል። ከፐረሻም ሌላ ምሁር ሮጀር ሽናይደር የተባሉት በኢትዮጵያ ምድር የተገኙት የሳባ ጽሑፍ በየመን ከተገኙት ጋራ በእድሜ እንደሚበልጡ እንጂ እንድሚያንሱ አረጋግጠዋል።
ለምሳሌ በሰሜን ኢትዮጵያ ጥንታዊ ከተማ የሃ የተገኘው የጽሐፍ ሰሌዳ በየመን ከተገኙት ሁሉ በእድሜ ይበልጣል። ( Encyclopaedia Brititanica, Cambridge 1911, Volume 24 ,P.628)
ኢትዮጵያዊዊ ሊቅ አስረስ የኔ ሰው ግእዝ የካም መታሳቢያ በተሰኘው ርእስ የዘረኞች ሴራና ተረት ተረት፣ የሳባውያን የአሠልጣኝነት ተልእኮ በአበሻ ምድር ውድቅ አድርገውታል። በደቡብ አረቢያ የሚገኙት ሐውልቶችና የጽሑፍ ሰሌዳዎች በኢትዮጵያ ነገሥታት ግዛታቸው የተመዘገቡ መሆናቸውን አስገንዝበዋል፡ የሳባ ፊደልና የሳባውያን ያሠልጣኝነት ተልዕኮ በአፍሪቃ ልፊፋ የጥቁርን ሕዝብ ታሪክና ሥልጣኔየለሽ ለማስመሰል የተሸረበ ያውሮፓ ቅኝገዥ ተሰፋፊዎች ሴራ መሆኑን አስምረውበታል።
ስለሆነም ወደ ኢትዮጵያ ምድር ከደቡብ አረቢያ የፈለሰ አበሻ የሚባል ነገደ የለም። ይልቅስ በተቃራኒው በዘመነ አክሱም አበሾች በየመን ሰለ መስፈራቸው በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል። የኢትዮጵያን ምድር በጥንት ዘመን አገሩ ፑንት፣ ሕዝቡን ደግሞ አበሻ ተብሎ የሚጠራውና የሚታወቀው በምደረ ግብፅ የፈርኦን ሥርዎ መንግሥት ታሪክ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ መሆኑ ቀደም ብሎ ተገልፇል።

## ዐማርኛ የግእዝ እኅት

ያማርኛ ቋንቋ የግእዝ ልጅ ነው ተብሎ በቤተ ክህነት ሰዎችና አንዳንድ የቋንቋ ሊቃውንት ነገባይ ሲነገር ቆይቷል። ዳሩ ግን መቼ እንደተጀመረ ጊዜውን ለይተው ሳያስውቁ ዐማርኛ በላስቶች ዘመነ መንግሥት ከብዙ ዓይነት ቋንቋ ተመርጦ የመንግሥት ቋንቋ እንደሆነና ልሳነ ንጉሥ መባሉን ይገልጻሉ።
የቤተ መንግሥቱ የመነጋገሪያና የሕዝቡ መግባቢያ ቋንቋ ዐማርኛ ሲሆን ግእዝ ግን የሥነ ጽሑፍና የቤተ ክህነቱ ዋና ቋንቋ ሆኖ እስከ 19ኛ ክፍለ ዘመን መቀጠሉ የተረጋገጠ ነው። ሆኖም ግን የቤተ መንግሥቱ ዜና መዋዕልና ታሪክ እንዲሁም የክርስትና ሃይማኖት መገልገያ የነበረው ግእዝ ከዳግማዊ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ዐማርኛ እየተካው እንደመጣ ይታወቃል። ቀደም ብሎም የግእዝ ቅኔና ሰዋሰው ትርጉም ማስተማሪያው ቋንቋ ዐማርኛ እንደነበር ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁብ እግዚ. (1961ዓ.ም) ዘግበውታል።
ብዙ የቋንቋ ሊቃውንት ለምሳሌ ዲልማን፣ ሮዲጀር ወዘተረፈ ዐማርኛ የግእዝ የቅርብ እኅት እንጂ ልጅ እንዳልሆነ ጽፈዋል። ይህም ትክክል ነው።
የዐማርኛ ቋንቋ ባሕርይ ከአገውኛና ሌሎች መሰሎች ጋራ 70 በመቶ እጅ ይዛመዳል።
የኢትዮጵያን ሕዝብ ሴማዊና ካማዊ ብሎ መከፋፈል የውሮፓውያኖች የቅኝ ገዥነት ተስፋፊዎችና ከፋፍለህ ግዛ ስልት ነው።
በሃይማኖት ሳቢያ የመጽሐፍ ቅዱሱን የብሉይ ኪዳን ዘፍጥረት የገሳዎች ትውልድ ሐረግ ትረካ ማለትም የኖህ ሦስት ልጆቹን የካም የሴምና የያፌትን ትውልዶች አስመልክቶ በቋንቋና የጎሣ ጥናትና ምርምር ሽፋን የኢትዮጵያን ልዩ ልዩ ነገዶችና ቋንቋቸውን የሚከፋፍሉብት ዘዴ ፍጹም የተዘበረቀና የተወናበደ ሆኖ ለፖለቲካ መሳሪያነት በጥንቃቄ ታስቦና ተሰልቶ የተደረገ እንደሆነ ግልጽ ነው። ነገር ግን በኢትዮጵያ ባሕልና እምነት ከጥፋት ውኃ በፊት የኦሪ ወይም የአራም ነገድ ከ4470 እስከ 3244 ዓ.ዓ ከኖረ በኃላ የነገደ ካም በኢትዮጵያ ከ2635 እስከ 1013 ዓ.ዓ ሲገዙ መኖራቸው ይተረካል። ከሁሉም በለይ ግን የግእዝ ቋንቋም በክብረ ነገሥት ሆነ በአንቀጸ ሃይማኖት ከቤተ ካም ወገን እንድሆነ ተመዝግቧል። አለቃ ታዬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ (አስመራ 1920) በተባለው መጽሐፋቸው ለምሳሌ ምዕራፍ ፮ ላይ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዋና ባባቶች የሴም ዘሮች ፮ ወገን ናቸው፡ እነዚህም አማራ፣ አገው፣ አስገዴ፣ ትግሬ፣ በቅላ፣ በደውና ሐባብ ናቸው።

በኢትዮጵያውያን ባሕል ነገደ አገው ሴማዊ ነው። ግእዝ፣ ሳባ፣ ቅብጥ፣ ኖባ ወዘተረፈ ሁሉ ኩሻዊ ቋንቋዎች ናቸው። ስለሆነም የኢትዮጵያን ቋንቋዎች ሴማዊና ኩሻዊ ብሎ መሸንሸንም ፖለቲካዊ ነው።

ታዲያ የመምሩ ሚስት እወቅሽ እወቅሽ ቢላት መጽሐፍ አጠበች እንዲሉ ምድረ የቋንቋ ሊቅ ተብዬ ጸዩናውያን ዘረኞች እነ ሊዎን በንዲርና ግብረ በላዎቹ አገር በቀል ጋጋኖዎች እነ ኃይሉ ፋሲስና (1983) ብጤዎቻቸው ሁሉ ስለ ዐማርኛ አመጣጥ የቀባጠሩትን መመልከት ያስፈልጋል።

የበንዲር መላምት ዋናው ይዘት ዐማርኛ በ4ኛው ክፍለ ዘመን የአክሱም መንግሥት ግእዝ ተናጋሪ መኮንኖችና ከአገውኛ ተናጋሪ ብዙ ወታደሮች እንዲሁም ከአባይ ሳሃራዊና ከኦሞዊ ቋንቋ ተናጋሪዎች ወደ ድቡብ ሲዘምቱ በተደረገው የዝነታ መስተጋብር (Pidginization) የተገኘ ነው ብለዋል። ያማርኛን ልዩ ባሕርያት ሁሉ ከተጠቀሱት ቋንቋዎች የተዘነቁ ናቸው በማለት አቅርበዋል። ያማርኛን ኢሴማዊነት በዚህ ዓይነት ከገለጹ በኋላ ደግሞ ዐማርኛ በግድ ሴማዊ አድርገው ይመድቡታል። ለምን?

የሴማዊነት ምደባ ያገኘው ከደቡብ አረቢያ ሥልጡን ሳባውያን ሴማዊ ቋንቋ፣ ፊደል፣ ሃይማኖት፣ ግብርና፣ ሕንፃ ግንባታ ወዘተረፈ ይዘው ቀይ ባሕርን ተሻግረው ጨለማውንና ኋላ ቀር ሥልጣኔየለሹን ጥቁር አፍሪቃን አሰለጠኑት፣ ወይም ሰፍረው ቅኝ አደረጉት ከሚለው የዘረኞች ርዕየት ነው። እንደሚናፈሰው በርግጥ ሳባዊያን በአፍሪቃ ስልጣኔ እምጪ ከሆኑ ለምን በመርዌ፣ በበርበራ፣ በዘይላ፣ በሞቃዲሾ፣ በሞምባሳ፣ በዛንጅባር ወዘተረፈ የሳባውያን ሕንፃ፣ ፊደል፣ ሃይምኖት፣ ግብርና ጥንታዊ ቅርሳ ቅርስ አልተገኘም?

አክሱምን ብቻ ለይተው የመረጡበትና በዚያ ሰፈሩ የተባለበት የፈጠራ ውሸት ምክንያቱ በኢትዮጵያ ከየመን የቀደመ፣ ከጥንት ግብፅና አፍሪቃ ጋራ የተዛመደ ሥልጣኔ ሳያቋርጥ በመገኘቱ ብቻ ነው።

በዚህ ዓይነት በግእዝ ቋንቋም ላይ የሚታየው "ኢሴማዊነት" በአፍሪቃ ምድር ከኩሻዊ ቋንቋ ጋራ ስለተዘነቀ ነው ይብሏል። ይህም ማወናበጃ የግእዝን ቅዳሚነትና አፍሪቃዊነት ለመሸፈን ታስቦ ነው። ግእዝና ዐማርኛ አረብኛንና እብራይስጥን፣ ሱርሱርትን፣ ከለዳዊን ይቀድማሉ።

የአፍሮ እሲያ ቋንቋ ምንጭ አፍሪቃ ነው። የደቡብ አረቢያም የአፍሪቃ ክፍል የኢትዮጵያ ጥንታዊ ግዛት ነበር።

የአረብኛ ፊደል ከግእዝና ከሳባ ጋራ ምንም ዝምድና የለውም። ያረብኛ የጽሑፍ ሰነድ ሰሌዳ የተገኘው በ512 ዓም ነመረ ከተባለው ከደማስቆስ በስተደቡብ ምሥራቅ ነው። የእብራውያን የሙሴ ሕግና ሃይማኖት በቃል ብቻ ሲተላለፍ ቆይቶ በአክሱም ዘመነ መንግሥት በአምስተኛው ክፍለ ዘመን ነው ያይሁዲዎች ታልሙድ በጽሑፍ በፍልስጥኤምና በፋርስ ግዛት ውስጥ የተከተበው። የእብራይስጥ ቋንቋ አናባቢ ምልክት ያገኘው በ9ኛው ክፍለ ዘመን ያክሱም መንግሥት በዛሳን ቤጃዎች ተወሮ ከወደቀ በኋላ ነው።

ግእዝ ማለት ቀዳሚ አንደኛ ነው፣ ፊደሉም እንዲሁ ቀዳሚነት ያለው ከጥንት ሂሮግሊፕስ በቀጥታ የወረደ እንጂ ከሳባ ተብዬ የተቀዳ አይደለም። በተቃራኒው ሳባ ከግእዝ ፊደል የተወረሰ ነው።

በየመን የነበሩት ሳባውያን ሚናናውያን ሒማራውያን ሁሉ ከነገደ ኩሽ ወገን የሆኑ በቋሚ ሰፋሪነት በግብርና የሚተዳደሩ ነበሩ እንጅ ዘላን ሴማዊ ጎሣዎችና ቋንቋ ተናጋሪዎች አልነበሩም።

...... ይቀጥላል

ከነ ፕሮፌሰር አዶ ሞሚና ይስማንና
ዶክተር ገብሬ ጉልቱ ግርማቸው
የአፍሪቃ ሥነ ቅርስና ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ዘርፍ